ታዬህ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብ ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTER OF FINANCE

ቁጥር / Ref. No. ሚ31/ኮ15/854

ቀን / Date 23/11/2017

ለገቢዎች ሚኒስቴር
ለጉምሩክ ኮሚሽን
ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ
አዲስ አበባ

በተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 570/2017 በአባሪ አንድ ከውጭ ወደ አገር ውስጥ ሲገቡ እና አገር ውስጥ ግብይት ሲፈጸምባቸው ከታክስ ነፃ የተደረጉ አቅርቦቶችን በተመለከተ በተራ ቁጥር 8 የበሰሉ ወይም የተዘጋጁ ምግቦች በሚለው ስር ከተዘረዘሩት ምግቦችና መጠጦች ውጭ ሌሎች የበሰሉ ምግቦችና መጠጦች ዝርዝር እንዲገለጽ ወይም በዝርዝር እንዲብራራ እና በተራ ቁጥር 11 ያልተዘጋጁ ሽንኩርት፣ ድንች እና አትክልቶች በሚል የተገለፀው ምን እንደሚያካትት ለአፈፃፀም ግልጽ ባለመሆኑ ማብራሪያ እንዲሰጠው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ በ19/10/2017 በቁጥር 10/7/15244/17 በተፃፈ ደብዳቤ ጠይቋል።

በተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 570/2017 አባሪ አንድ አንቀጽ 8 ላይ የተዘረዘሩትን የተወሰኑ "የተዘጋጁ ምግቦች/መጠጦች" ከታክሱ ነፃ ለማድረግ የተመለከተው ድንጋጌ ሊተረጎም የሚገባው በጥንቃቄ ነው። ይህ ድንጋጌ እንጀራ፣ ዳቦ እና ወተት ከታክሱ ነፃ የሆኑ እቃዎች እንደሆኑ ይዘረዝራል። የህግ አውጪው ዓላማም ከታክስ ነፃ መሆኑ እነዚህን ሶስት መሠረታዊና አስፈላጊ የሆኑ የስነ-ምግብ ጠቀሜታ ያላቸውን ምግቦች ብቻ እንዲያካትት ነው። በመሆኑም በአንቀጽ 8 ስር ያለው ዝርዝር የተሟላ (exhaustive) ተደርጎ መወሰድ አለበት። ሌሎች የተዘጋጁ ምግቦች ወይም መጠጦች በዚህ የታክስ ነፃ ወሰን ውስጥ አይገቡም።

በሌላ በኩል በደንቡ አባሪ አንድ አንቀጽ 11 ላይ "ያልተዘጋጁ ሽንኩርት፣ ድንች እና አትክልቶች" ከታክሱ ነፃ እንደሆኑ ይደነግጋል። በዚህ ድንጋጌ የቃላት አጠቃቀሙ ይበልጥ ክፍት የሆነ አካሄድን ያመለክታል። ሽንኩርት እና ድንች በግልጽ የተጠቀሱ ቢሆንም፣ "አትክልቶች" የሚለው ቃል ደግሞ የተሟላ ዝርዝርን ከማመልከት ይልቅ ምሳሌያዊነትን (illustrative) ለማመልከት ዓላማን ያነገበ ነው። ለአፈጻጸም ዓላማ ይህ ማለት የታክስ ነፃ መሆኑ በጥሬ፣ ሙሉ እና ያልተቀነባበረ (unprocessed) መልክ የሚሸጡ ወይም የሚገቡ ሁሉንም አትክልቶች ያካትታል። ይህም ምንም ዓይነት ፍራፍሬዎችን ሳይጨምር እንደ ቲማቲም፣ ጎመን፣ ካሮት፣ ሰላጣ፣ ቃሪያ እና መሰል ምርቶችን የሚሸፍን ሲሆን፣ እነዚህም ሳይበስሉ፣ ሳይቆረጡ፣ ሳይቀዘቅዙ፣ ሳይታሸጉ ወይም በሌላ መልኩ ዝግጅት ወይም የማቀነባበር

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብ ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTER OF FINANCE

ቁጥር / Ref. No. _____

ቀን / Date _____

ሂደት ካልተደረገባቸው ነው። የዚህ ህግ አላማ ተፈጥሯዊ የሆኑ አስፈላጊ የምግብ ግብዓቶች ከታክስ ነፃ እንዲሆኑ ማድረግ ነው። በመሆኑም በኢትዮጵያ በብዛት ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም ጥሬ አትክልት ያልተቀነባበረ እስከሆነ ድረስ በዚህ አንቀጽ ስር ከታክሱ ነፃ ተደርጓል።

ስለዚህ በአንቀፆቹ ላይ ከዚህ በላይ የተሰጠውን የሕግ ማብራሪያ መሰረት በማድረግ ማስተናገድ የሚቻል መሆኑን እናሳስባለን።

ከሠላምታ ጋር

ኢዮብ ተካልኝ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ግልባጭ፡-
ለታክስ ፖሊሲ መምሪያ
ገንዘብ ሚኒስቴር

ARK/LETTER